# የእንቅልፋሞችና የወኔ ቢሶች አመራር

የሐገራችን የፖለቲካ አካሄድ ከቀን ቀን እየከፋ እንጂ እየተሻሻለ እንዳልሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

መቼም የፖለቲካ "ሀሁ" ለገባው ብልጽግና ፓርቲ ሲቋቋም ዋና አላማው አማራውን ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት እንደሆነ ይታመናል ። ነገር ግን ይህንን በምንናገርበት ወቅት አንዳንድ ግለሰቦች ባንድም ሆነ በሌላ ምክን ያት ጥርጣሪያችንን ፣ አንድም ከብሄረተኝነት አሊያም ከዶ/ር አብይ ጥላቻ የተነሳ አድርገው ሞግተውናል ፣ ሆኖም ግን "ጊዜ ለኩሉ" እንዳለው ፣ ጊዜ ሁሉን ጥርጣሬያችንን እውን እንደሆነ አስመስክሯል ብለን እናምናለን ።

የሰኔ 15ቱ ግድያ ከመፈጸሙ በፊት በወሎ ወልድያ ዶር አብይ ዶር አምባቸውና ዶር ደብረፂዮን ባሉበት የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠውን ገንዘብ የክልል አስተዳደሮች ልዩ ኃይልና ሚሊሺያ ማሰልጠኛ ፣ የጦር መሳሪያ መግዣ አድርገውታል ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል ። *እዚህ ላይ የዶር አብይ ክልል ለ 29 ጊዜ ልዩ ኃይልና ሚሊሺያ እንዳሰለጠነ አማራው ግን ገና ማሰልጠን ሲጀምር እንደመቱት እንዳትዘነጉ ለማሳሰብ እወዳለሁ ።* ይህንን ንግግር በተናገሩ በጥቂት ቀናት ልዩነት ውስጥ በአማራ ክልል የከፍተኛ አማራሮች ግድያ ተፈጽሟል ።

ይህ ግድያ በተፈጸመ በወሩ የዶ/ር አብይ የረዥም ጊዜና በጣም የቅርብ ጓደኛ የሆነ እንዲሁም በቤተ መንግሥቱ የቅርብ የፖለቲካ አማካሪ ሆኖ የሚሰራው ልክ እንደ ዶ/ር አብይ በኢንሳ ከዶ/ር አብይ ስር በመሆን የኢሕአዴግን (ወያኔን) በማገልገል የሚታወቁትን አቶ ተመስገን ደሳለኝን የአማራ ክልል ምክትል አስተዳዳሪ በማድረግ አዴፓ ሳይሆን ኦዴፓ እንደሾማቸው ይታወቃል ። ይህ በንዲህ እንዳለ አሿሿሙ ትክክል እንዳልሆነ በርካታ ኢትዮጵያውያን ድምፃቸውን ቢያሰሙም ሰሚ ጆሮ አልተገኘም ።

አቶ ተመስገን ደሳለኝን ምንም እንኳን የአማራ ክልል አስተዳዳሪ ቢሆኑም እንደሚወራው በየቀኑ የአማራ ክልል ዋና ጽ/ቤት ካለበት ከባሕርዳር አዲስ አበባ በመመላለስ በየለቱና በየሰዓቱ በአማራ ክልል የተደረገውን ለዶ/ር አብይ ለማቀበል የአማራውን ሀብትና ንብረት በማባከን በቀን ሁለቴ የኢትዮጵያ አየር መንገድን በመጠቀም ውሎቸው ባሕርዳር አዳራቸው አዲስ አበባ እንደሆነ በሰፊው ቢነገርም አድማጭ ተገኝቶ እንዲታረም አልተደረገም ።

ወደ ብልጽግና ፓርቲ አመሰራረት ስንመለስ የዚህ ፓርቲ ዋና አመሰራረቱ አማራውን አለመሪ ማስቀረትና አማራውን ለማዳከም ነው ስንል አለምክንያት አልነበረም ፣ እንደሚታወቀው የዚህ ፓርቲ ምስረታና መተዳደሪያ ደንብ እረቂቅ በማያሻማ አማርኛ በአንቀፅ "5" የፓርቲው የስራ ቋንቋቋዎች በሚለው ርዕስ ስር እንዲህ ሲል አስቀምጦልናል ፣ *"ሐ. ክልሎችና የአካባቢ ቅርንጫፍ ፓርቲ ፅ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የስራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም አለባቸው"* ።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው ብለን እራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው ፣ በዚሁ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ፯ "ሐ" ላይ የተጠቀሰው የስራ ቋንቋዎችን ታሳቢ በማድረግ ከሚለው ወረድ ይልና አንቀጽ 7 የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በሚለው ላይ እንዲህ ሲል አስፍሮታል :- *" ፫) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፓርቲው በዞን ፤ በወረዳና በቀበሌ እንዲሁም እንደአስፈላጊነት ኢትዮጵያውን በብዛት ባሉባቸው ውጭ አገራት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል"* ። ይለናል ።

እዚህ ላይ አንባቢያን በንጹህ ህሊና እንዲገነዘቡልኝ የምፈልገው በሐገራችን ያሉ ሕዝቡን ሳይሆን ከመቶ በላይ ያሉና የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ብንመለከት ሙሉ ለሙሉ ማለት ባልችልም ከመቶ ሰማንያ የሚሆነው የፖለቲካ ድርጅት አባል አማርኛ ማንበብና መፃፍ ፣ መናገርም እንደሚችል አጠያያቂ አይሆንም ። በአንፃሩ ግን ወደ አማራው ድርጅት ስንሄድ ባንድም ይሁን በሌላ መንገድ አማርኛ ለረጅም ዘመናት የሐገራችን ብሄራዊ ቋንቋ በመሆኑ በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ከሰሜን እስከ ደቡብ ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ባራቱም አቅጣጫ በሰፊው የሚነገርና ዋነኛ የመግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ ምክንያት አማራውን ለሚወክሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ሌላ ሁለተኛ የሐገሪቱን ቋንቋ እንዳይማሩ ወይንም እንዳያውቁ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው ሆኖ ሆኖም ግን የሚናገሩ አይኖሩም ባይባልም ቢኖሩም ቁጥራቸው ከመቶ አስር ፐርሰንት በታች ሊሆን እንደሚችል ከማንም የተሰወረ አይሆንም ። ስለሆነም በአዲሱ የብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ

መሰረት በማንኛውም የጽ/ቤቱ አገልጋይ በክልሉ ከሚነገረው ቋንቋ በተጨማሪ በሁለተኛ ደረጃ ሌላ በሐገር ውስጥ የሚነገር ቋንቋን መናገር እንዳለበት ይደነግጋል ፣ ይህ ማለት ደግሞ ከአማርኛ ተናጋሪው ተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማግኘት አዳጋች እንደሆነ የሚያውቀው ብልጽግና የአራሱ ብሔር የሆኑና አማርኛ መናገር የሚችሉትን ኦዴፓዎች በአማራው ክልል ማስቀመጥ ግድ ይላል ። አሁን ተቃውሞ ማስነሳትም አይቻልም ክልሉን የሚያስተዳድረው “አዴፓ” ሳይሆን “የአማራው ብልጽግና” ስለሆነ ማለት ነው ፣ አሁን አዴፓ የሚባል ነገር ስለማይኖር “የአማራው ብልጽግና” ደግሞ የሚመራው በብልጽግና ማዕከላዊ አመራር ይሆናል ። ከላይ ለማብራራት በተሞከረው መሰረት አሁን አዴፓ ግብአተ መሬቱ ተፈጽሞለት አዲሱ የአማራው ክልል ገዢ ኃይል ባደባባይ ብልጽግና በስውር ኦዴፓ ነው ማለት ነው ።

ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው ሰሞኑን በአማራ ክልል የተደረገው ሹመትን ወይንም የሹም ሽር መመልከት ከበቂ በላይ ነው ፣ ለአማራው በጽናትና በብቃት ይሟገታሉ ተብለው ባብዛኛው ዘንድ የሚታመኑትን አቶ ዮሃንስ ቧያለውን ከክልሉ አንስተው ምንም ለአማራው አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የማይችሉበት ስፍራ በመመደብና ከክልላቸው በማራቅ ዋጋቢስ አድርገው ለማስቀመጥ መሞከራቸው ሳያንስ በዶ/ር አብይ ተላላኪና የአማራው ክልል ምክትል አስተዳዳሪ ተብዬ አቶ አቶ ተመስገን በአቶ ዮሃንስ ቧያለውና ሌሎችም ላይ የተደረገውን ሹመት ይሁን ሽረት ተበዳዮቹ እነ አቶ ዮሃንስ በደስታ እንደተቀበሉትና እንዲያውም የክልሉ ፖለቲካ እንደሰለቻቸውና እንዳደከማቸው በተደረገውም ለውጥ እጅግ ደስተኛ መሆናቸውን አይናቸውን በጨው ታጥበው በተለመደው ኢሐዴጋዊ ቅጥፈት በቀጠፉ ማግስት አቶ ዮሃንስ ቧያለው ስለተሰጣቸው ሹመት (ሹም ሽር) እንደማንኛውም ዜጋ በብዙሐን መገናኛ እንደሰሙና ሹመቱንም (ሽረቱን) እንደማይቀበሉ በጨዋ አማርኛ የአዴፓ ሙታን እነ ደመቀ መኮንን ፣ ገዱ አንዳርጋቸው ፣ ተመስገን ደሳለኝንና ሌሎችንም የኦዴፓ አፋሽ አጎንባሾችን ሊገባቸው በሚችል አማርኛ ቅሬታቸውንና የሴራ ፖለቲካቸውን አጋልጠው አልፈዋል ።

እንግዲህ ብልጽግና አማራውን ማዳከምና ማፍረስ ፣ አቅመቢስ ማድረግ ነው ዋና ተግባሩ ስንል አለምክንያት እንዳልሆነ የሰሞኑ የነ አብይ ድራማ ከበቂ በላይ ማስረጃ ይሆነናል ። እዚህ ላይ ሌላ ተጨማሪ ለማከል ያህል ደግሞ ለጊዜው ስማቸውን የማላስታውሳቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑ ዶ/ር የአማራ ክልል ምክትል አስተዳዳሪ ሆነው ተሾመዋል ፣ መሾማቸው መልካም ብንልም ነገር ግን እነሱ ባለጌዎቹ እንደነገሩን ዶ/ሩ ምንም አይነት የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳልሆኑና ለክልሉ ይሄ ማለት ትልቅ ለውጥ እንደሆነ ሳያፍሩ ነግረውናል ፣ እውነት ሐገርና ክልል በፖለቲከኞች በሚመራበት ምንም የፖለቲካ ትስስር ፣ ከማንኛውም ፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌለው በክልሉ ማስቀመጥ ማለት ምን ማለት ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል ። መሪው የፖለቲካ ድርጅቱ እስከሆነ ድረስ ዶ/ሩ ጉዳይ አስፈጻሚ እንጂ ምንም ማለት አይደለኡም ማለት ነው ፣ ዶ/ሩ አሁንም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ስላልሆኑ በማናቸውም የፖለቲካ ስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ ተሳታፊ አይሆኑም ማለት ነው ፣ ስለሆነ ባለጌዎቹ የሚንግሯቸውንና እነሱ እንዲሆን የሚፈልጉትን በክልሉ የስራ አስፈጻሚ ናቸው ማለት ነው ። እንዲህ ነው እንግዲህ ብልጽግና የአማራው ጠላት የአማራው ገዳይ ነው የምንለው ። ለዚም ነው የእንቅልፋሞችና የወኔ ቢሶች አመራር አማራውን እያስጠቃ ነው የምንለው ።

አማራ ንቃ !!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

ታዛቢው

February 27, 2020